# የቤት ባለቤትነት ፕሮግራም መስፈርቶች

**የዋሽንግተን ዲሲ ሀቢታት ፎር ሁማኒቲ** ቀላል፣ በቂ የሆነ ቤትን ከሚፈልጉና መስፈርት ከሚያሟሉ ገዥዎችጋር በመተባበር አነስተኛ ገቢ ላላቸው የሚውሉ ቤቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ያቀርባል። በሚለገሱ ገንዘብና እቃዎች በበጎ ፈቃድ የተገነቡ ቤቶችን ያለምንም ትርፍ እንሸጣለን። እርዳታን ሳይሆን አቅምን እናቀርባለን።

## አጠቃላይ መስፈርት

አመልካቾች የሚከተሉትን **በሙሉ ማሟላት ይኖርባቸዋል**:

- ለመጀመሪያ ጊዜ ቤት የሚገዛ (በባለፉት 3 ዓመታት ውስጥ ሪል ኢስቴት ያልነበረው)፤
- ዲሲ ውስጥ ለአንድ ዓመት የኖረ ወይም ደግሞ ዲሲ ውስጥ ለሁለት ዓመት የሰራ፤
- የዩ ኤስ ዜጋ ወይም ቋሚ ነዋሪ።

## ፍላጎት

አመልካቾች ከሚከተሉት **ቢያንስ አንዱን ማሟላት ይኖርባቸዋል**:

- አስጊ (ጤናማ) ያልሆነ አካባቢ፤
- በጊዜያዊ የመኖሪያ ቤት የሚኖር፤
- ድጎማ በሚደረግበት ቤት ውስጥ የሚኖር ወይም በቤት ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ የሚሳተፍ፤
- ከመጠን በላይ መጨናነቅ፤
- የኪራይ ጫና (ከ30% በላይ የሚሆነውን ወርሃዊ ገቢ ቤት ኪራይ ላይ የሚያውል)፤
- ማሞቂያ፣ የኤሌክትሪክ፣ የእንጨቱ ወይም አሰራራዊ ችግሮች።

## የመክፈል አቅም

አመልካቾች የሚከተሉትን **በሙሉ ማሟላት ይኖርባቸዋል**:

- ገቢው ከ30-60%* የአማካይ አጋማሽ ገቢ (አቬሬጅ ሚዲያን ኢንካም) መካከል መሆን (የቅጥር ደሞዝ እና ወይም ቋሚ ጥቅማ ጥቅሞችን ሊያካትት ይችላል)፤
- በአሁኑ ስራቸው ቢያንስ ለ6 ወር ያክል የቆዩ መሆንና በስራዎች መካከል ከ2 ወር ያልበለጠ ጋፕ የሚያሳይ የ2 ዓመት የሥራ ታሪክ፤
- በራስ ተቀጥረው የሚሰሩ ከሆነ በሰነድ የተረጋገጠ የ2 ዓመት ቋሚ ገቢ ያለው መሆን፤
- አማካይ የክሬዲት ውጤት 620 እና ከዛ በላይ፤
- ካልተከፈሉ ተሰብሳቢ፣ ፍርዶች እና ከዕዳ ማስያዣዎች ነጻ የሆኑ የክሬዲት ሪፖርቶች፤
- የክሬዲት ሪፖርቶች ለባለፉት 3 ዓመት ኪሳራን ወይም ደግሞ በ7 ዓመት ውስጥ ፎርክሎዥሮችን ማሳየት የለባቸውም፤
- 3ኛ ወገን ከፋይ ማግኘት
- ጠቅላላ ገቢው ለቤት ወጭ ከሚውለው ሲነጻጸር ከ30% ያነሰ ከሆነ (ፍሮንት ኤንድ ዴብት ቱ ኢንካም ሬሽዎ) እና 43% በባክ ኤንድ ከሆነ፣
- $500 በዕለቱ የባንክ መግለጫዎች (ስቴትመንትስ) ማሳየት እና ባለፉት ሁለት ወራቶች ውስጥ ምንም አይነት ካለው የብር ገንዘብ በላይ ወጭ ያልተደረገበት (ኦቨር ድራፍት)።

| የቤተሰብ ብዛት | ዓመታዊ የገቢ መጠን * | | ወርሃዊ የገቢ መጠን * | |
|---|---|---|---|---|
| | አነስተኛ | ከፍተኛ | አነስተኛ | ከፍተኛ |
| 1 | $ 22,470 | $ 44,940 | $ 1,872 | $ 3,745 |
| 2 | $ 25,650 | $ 51,360 | $ 2,140 | $ 4,280 |
| 3 | $ 28,890 | $ 57,780 | $ 2,407 | $ 4,815 |
| 4 | $ 32,100 | $ 64,200 | $ 2,675 | $ 5,350 |
| 5 | $ 34,680 | $ 69,360 | $ 2,890 | $ 5,780 |
| 6 | $ 37,260 | $ 74,520 | $ 3,105 | $ 6,210 |
| 7 | $ 39,810 | $ 79,620 | $ 3,317 | $ 6,635 |
| 8 | $ 42,390 | $ 84,780 | $ 3,532 | $ 7,065 |

**ልዩ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ*

## የትብብር ፈቃደኝነት

አመልካቾች የሚከተሉትን **በሙሉ ማሟላት ይኖርባቸዋል**:

ሁሉም የፕሮግራም ተሳታፊዎች ከ200 እስከ 300 ሰዓት የሚደርስ "የጉልበት አስተዋጽኦ (ስዌት ኢኩቲ)፣" ማድረግ ወይም የበጎ ፈቃድ ስራ ውስጥ መሳተፍ ይኖርባቸዋል። ይህም በኮንስራክሽን ሳይቱ መስራትን፣ የቤት ባለቤትነትና የገንዘብ አያያዝ መሰረታዊ የትምህርት ክፍሎችን መከታተል፣ እና ወይም ቢሮ ውስጥ ወይም በልዩ ዝግጅቶች ላይ በበጎ ፈቃድ ማገልገል። ተሳታፊዎች ከዲሲ ሀቢታት ጋር በቀጣይነት በመነጋገር፣ በቀጠሯቸው አማካኝነት በመገኘትና ከቤት ባለቤትነት ጋር የሚመጡ ሃላፊነቶችን በመቀበል ለመተባበር ፈቃደኛ እንደሆኑ ማሳየት ይኖርባቸዋል።

EQUAL HOUSING OPPORTUNITY

የዋሽንግተን ዲሲ ሀቢታት ፎር ሁማኒቲ ይሆናል ተብሎ በተገመተ ወይም በተረጋገጠ ዘር፣ ቀለም፣ ሃይማኖት፣ የትውልድ ሃገር፣ ጾታ፣ ዕድሜ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ ጾታዊ ማንነት ወይም አገላለጽ፣ ግለሰባዊ ገጽታ፣ የቤተሰብ ሁኔታ፣ የቤተሰብ ሃላፊነቶች፣ ምዝገባ (ማርቲኩሌሽን)፣ ፖለቲካዊ ትስስር፣ ጀነቲካዊ መረጃ፣ አካል ጉዳተኝነት፣ የገቢ ምንጭ ወይም የመኖሪያ ወይም ንግድ ቦታን መሰረት በማድረግ አድሎ አይፈጽምም።

2115 Ward Ct NW, Suite 100 · Washington, DC 20037 · የቢሮ ስራ አስኪያጅ /የቤት ፕሮግራሞች ተባባሪ: ማንዲ ጃንሰን ስልክ: (202) 882-4600
የውስጥ መስመር 200 · ፋክስ: (202) 882-9343 · ኢሜይል: Mandy.Jansen@dchabitat.org